የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.36
ADDIS ABABA 10th February, 2016

አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፯/፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የዲፕሎማቲክ ፓስፖርቶች ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን የትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……….ገጽ ፰ሺ፯፻፺፬

Proclamation No. 927/2016

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Mutual Abolition of Visas for Holders of Diplomatic Passports Ratification Proclamation ……………………………………..…Page 8794

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፯/፪ሺ፰

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የዲፕሎማቲክ ፓስፖርቶች ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገውን የትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፑብሊክ መንግስት መካከል የዲፕሎማቲክ ፓስፖርቶች ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገው የትብብር ስምምነት ታህሳስ ፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም በኢስታንቡል የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## Proclamation No.927/2016

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TURKEY ON MUTUAL ABOLITION OF VISAS FOR HOLDERS OF DIPLOMATIC PASSPORTS</u>**

WHEREAS, the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Mutual Abolition of Visas for Holders of Diplomatic Passports has been signed in Istanbul on the 16th day of December, 2011;

WHEREAS, the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 14th day of January, 2016;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የዲፕሎማቲክ ፓስፖርቶች ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን የትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፯/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ታህሳስ ፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም የዲፕሎማቲክ ፓስፖርቶች ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት በኢስታንቡል የተፈረመው የትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

## ፫. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይህን ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Mutual Abolition of Visas for Holders of Diplomatic Passports Ratification Proclamation No.927/2016".

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey on Mutual Abolition of Visas for Holders of Diplomatic Passports signed in Istanbul on the 16th day of December, 2011, is hereby ratified.

## 3. Responsibility of the Ministry of Foreign Affairs

The Ministry Foreign Affairs in collaboration with the relevant organs is hereby empowered to implement this Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, 10th day of February, 2015.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**